
# የሽግግር ዕቅድ



## ለወደፊት ትኩረት-የተደረገበት

### ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (DR. MELANIE KAY-WYATT)

የትምህርት ቤቶች ጠቅላይ-ሥራ አስኪያጅ
የ2023-24 የትምህርት ዓመት




Alexandria City Public Schools
1340 Braddock Place
Alexandria, VA 22314

# ማውጫዎች

03 ስለ ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt)

04 ዓላማ/Purpose

05 የሽግግር ቀደምት-ነገሮች

06 የፕሮግራሞች ትኩረት

07 ተሣትፎ እና ግንኙነት



# ስለ ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት

# (DR. MELANIE KAY-WYATT)

ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt)፣ የተረጋገጠላቸው የትምህርት-አሰጣጥ መሪ ሲሆኑ፣ በሙያተኛነታቸው የቀደመ-መነሻቸው/background - ሰፊ-ልምድን ባካበቱበት በማስተማር እና መማር መስክ እና በአጠቃላይ በኮመንዌልዝ (Commonwealth) ውስጥ፣ በበርካታ ዓይነት የስራ-ድርሻዎች እና አቀማመጦች ውስጥ -የሰሩ-ናቸው።



በሜይ (May) 4 ቀን 2023 ላይ፣ የትምህርት ቤት ቦርዱ - ዶ/ር ሜላኒ ኬይ-ዋየት (Dr. Melanie Kay-Wyatt) እንደ አዲስ ቋሚ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ ሆነው ለአሌክሳንድርያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ከጁላይ (July) 1 ቀን 2023 ጀምሮ በማገልገል ስራቸውን እንደሚቀጥሉ አስታውቋል። ይህም-በጁላይ (July) 28 ቀን 2022 ላይ የአሌክሳንድርያ ከተማ ትምህርት ቤት ቦርድ፣ ኬይ-ዋየት (Kay-Wyatt)ን እንደ-ጊዜያዊ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ አድርጎ ስራቸውን ከሴፕቴምበር (Sept.) 1 ቀን 2022 ጀምሮ-ጀምረው በተሾሙበት ተከታዩ የስራ-ድርሻ ሰርተው-ነበር። ይህ ሹመት፣ ከዚያ-ቀደም በአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools) ውስጥ የነበራቸው የስራ-ድርሻ ተከትሎ የመጣ-ነበር።




በጁላይ (July) 1 ቀን 2021 ላይ፣ ዶ/ር ኬይ-ዋየት (Kay-Wyatt) በACPS ውስጥ፣ የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools) በሰው-ኃይል አስተዳደር (human resources) ውስጥ፣ እንደ ዋና-ዳይሬክተር ሆነው የስራ-ጉዞአቸውን የጀመሩ-ሲሆን፤ ጠንካራ-ስራቸውን እና ለሚያገለግሏቸው ያላቸውን ቁርጠኝነታቸው እውቅና-በመስጠት፣ ወደ የሰው-ኃይል አስተዳደር (human resources) ዋና-ሹምነት - በACPS ውስጥ በ2021 ከጀመሩበት ጊዜ፣ በአንድ-ዓመት ጊዜ ውስጥ ብቻ የስራ-ዕድገት ያገኙ ናቸው።

የላቀ-ደረጃ ያለው የድርጅታዊ-አሰራር፣ ግንኙነት/communication-የማድረግ ችሎታ እና የደንበኛ-አገልግሎት አሰጣጥ ችሎታቸው፤ የትምህርት ቤት ቦርድ ቀደምትነት ከሚሰጣቸው ነገሮች እና የACPS ዓላማ እና ራዕይ ከሆነው ከ*'2025 የስልታዊ ዕቅድ (Strategic Plan): ፍትሃዊ-እኩልነት ለሁሉም/Equity for All'* ጋር ጎን-ለጎን ሆኖ በሚሰራው የACPS ማህበረሰብ-ውስጥ በስኬታማነት አገልግለዋል። የኬይ-ዋየት (Kay-Wyatt) በየመምሪያው ውስጥ ያላቸው ትብብር፣ እንዲሁም ከውጪ ባለድርሻ-አካላት (external stakeholders) ጋር፤ ለሁሉም ትምህርት ቤቶች በትምህርት-አሰጣጥ እና በሠራተኛ-አቀጣጠር አዋጭነት ላይ ለመርዳት፤ የተማሪዎቻችን ትምህርት እንዲቀጥል ለማረጋገጥ የትምህርት ቤት ስርዓቱን በብቃት-ለማስቻል፣ በተለይ-ደግሞ በዓለም ወረርሽኝ COVID-19 ተከስቶ አስቸጋሪና-ፈታኝ ጊዜያቶችን በነበሩበት ጊዜ፤ የትብብር-ስራን ሠርተዋል።

ኬይ-ዋየት (Kay-Wyatt)፣ በቢዝነስ አስተዳደር/business administration፣ ከሜሪ ዋሽንግተን ኮሌጅ የባችለር ዲግሪ፣ በትምህርት ሣይንስ/science in education - ከኦልድ ዶሚኒየን ዩኒቨርስቲ፣ ማስተርስ፤ እንዲሁም በተጨማሪ በትምህርት አመራርነት (Educational Leadership) ከሜሪ ዋሽንግተን ዩኒቨርስቲ/University of Mary Washington የማስተር ኦር ኢዱኬሽን (Master of Education) ያላቸው ናቸው። የኬይ-ዋየት (Kay-Wyatt) ዶክትሬት፣ ከቨርጅኒያ ኮመንዌልዝ ዩኒቨርስት (Virginia Commonwealth University) በቅድመ ማንበብና መፃፍ ቡድኖች ግምገማ ማዕከል-ያደረገ እና በ'Title I' በትምህርት ቤት-አቀፍ እና ዒላማ-የተደረገበት እገዛ-ሰጪ ፕሮግራሞች (schoolwide and targeted assistance programs) ለትምህርት ቤቶች ባላቸው አስተዋጽዖ ላይ ምርምራቸውን-ሰርተዋል።

ልምድ-እንዳለው ትምህርት-ሰጪ እና አስተዳዳሪ ሆነው፣ ኬይ-ዋየት (Kay-Wyatt) የስራ-መስካቸውን የጀመሩት እንደ የልዩ ትምህርት (special education) አስተማሪ-ሆነው፣ በኩልፔፐር (Culpeper)መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት ውስጥ እና ቀጥለውም ወደ ፍሬደሪክስበርግ ቨርጂኒያ (Fredericksburg, VA) ሄደው፣ በኋላም እንደ መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት ረዳት ርዕሰ መምህር መጀመሪያ-ከሰሩ በኋላ፣ ቀጥሎም በዋከር-ግራንት (Walker-Grant) መካከለኛ ደረጃ (Middle) ትምህርት ቤት ውስጥ የርዕሰ-መምህርነት ቦታቸውን ወስደዋል። በዊሊያም እና ሜሪ (William & Mary) ኮሌጅ እና በሸነንዶሃ ዩኒቨርስቲ (Shenandoah University) እንደ ፕሮፌሰር ሆነው ልምድ-ያካበቱም-ሲሆን፣ በትምህርት ቤት ማሻሻያ ላይ ትኩረት አድርገው - በመማሪያክፍል አስተዳደር ቴክኒኮች እና በሰው-ኃይል አስተዳደር አመራርነት ላይ፣ ትምህርት-ሰጥተዋል።



የኬይ-ዋየት (Kay-Wyatt) ጠንካራ አስተዳደራዊ ብቃቶች በሚገባ-የተቀረጹት በስፓትስቬኒያ (Spotsylvania) ካንውንቲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ እንደ የሰው-ኃይል አስተዳደር (Human resources) ዳይሬክተር ሆነው-ባገለገለቡት ጊዜ እና ከዚያው-ጎን ፕሬዚዳንትነታቸው ጊዜ፤ እና የዓለም-አቀፍ የትምህርት አባልነት ድርጅት (international education membership organization)፣ ASCD እንደ የቀድሞ የቦርድ ሊቀመንበርነት ጊዜያቸው ነው። በስፓትስቬኒያ (Spotsylvania) በሰው-ኃይል (human resources) አስተዳደር የስራ-ድራሻቸው ውስጥ፣ የቅጥር-ሁኔታን እና ከፍተኛ-የብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ያላቸውን እና እርዳታ-ሰጪ ተቀጣሪዎች ጠብቆ-በማቆየት ላይ ከሚሰሩት-ስራ በተጨማሪ፣ ለ' Future Educators Academy' ዕቅድ-ማስፈጸሚያ በተሣካ-ሁኔታ የቀረጹ እና የባለ-ሁለት ምዝገባ (Dual Enrollment) ፕሮግራሞችን አግዘዋል። ኬይ-ዋየት (Kay-Wyatt) በተጨማሪም፤ በASCD ውስጥ፣ የስልታዊ የበጀት ዳግም-ማደረጃጀቶችን (strategic reorganizations of budget) እና የሠራተኛ-አቀጣጠር ላይ እና ስልታዊ ተቀዳሚነት ያላቸውን ነገሮች ለማግኘት በገንዘብ እና ቢዝነስ ብልሃት ላይም የስራ-እውቀታቸውን አሳይተዋል። በሕዝብት ትምህርት አገልግሎት ዓመቶቻቸው ሁሉ-ውስጥ፣ ኬይ-ዋየት (Kay-Wyatt) ጥልቅ፣ ግልጽ የተማሪ እና ሠራተኞ ፍላጎቶች ላይ ግንዛቤን ያሳዩ፣ እንዲሁም ከውስጥ ባለድርሻ-አባላቶች (internal stakeholders) ጋር፣ ሌላ የትምህርት ቤት ክፍሎች/divisions፣ እና የውጪ ኤጀንሲዎች ጋር ሆነው ክፍል-አቀፍ/divisionwide ፍላጎቶችን በኩልነት ምላሽ-በሚሰጠው ሁሉን-አቀፍ ዕቅዶችን እና ፖሊሲዎችን ለማበረታታ፣ በቅርበት አብሮ-ለመስራት ከፍተኛ-የሆነ ትጋትን አሳይተዋል። እነዚህ ማሳያ ባህሪያቶቻቸው፣ በACPS ማህበረሰብ ተማሪዎች፣ ቤተሰቦች፣ እና ሠራተኞች ላይ - በአዲስነት በተሾሙበት የቋሚ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅነት የስራ-ድርሻ ላይ ሆነው የትምህርት ቤት ክፍሉ/divisionን በሚመሩበት ጊዜ፤ አዎንታዊ የሆነ አስተዋጽዖ (positive impact) እንዳለው፣ ጥርጥር-የለውም። ኬይ-ዋየት (Kay-Wyatt)፤

ሁለት ትልቅ-ሴቶች ልጆች ያደረሱ፣ ኩሩ-የሆኑ እናትም-ናቸው።

# ዓላማ/PURPOSE

እንደ መጪው ቋሚ ጠቅላይ-ስራ አኪያጅነት፣ የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤት (Alexandria City Public School) ቦርድ፤ ሁሉም ተማሪዎች የሚያስፈልጓቸው ነገሮች ሁሉ ተሟልተው መገኘቱን ለማረጋገጥ እና የትምህርት ቤት ክፍሉ/divisionን ወደ ከፍተኛ እድገት እና ስብጥር-ያለው አሰራር በማዘጋጀት፤ የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools (ACPS) ያለውን የቆየ-ውርስ እንዲቀጥለ ለማድረግ-ኃላፊነት ሰጥቶኛል።

በጊዜያዊ ጠቅላይ-ስራአስኪያጅነቴ ወቅት፤ በACPS ትኩረት በሚያደርግባቸው ነገሮች ላይ እና *የACPS 'ስልታዊ ዕቅድ (Strategic Plan): Equity for All'* በመቀጠል-ማስፈጸም ላይ አተኩሬ-ነበር። ይህ ትኩረት፣ ወደ ቋሚ ስራ-አስኪያነት የስራ-ድርሻዬ በምሸጋገርበትን ጊዜ የሚቀጥል ሲሆን፣ ይህም ስብጥር-ያለውን እና ንቁ-የሆነው ማህበረሰብ እያሳተፉ አቅፎ-ለመጓዝ ያለኝን-ቁርጠኝነት ጠብቄ-በመቆየት ይሆናል።

የዚህ የሽግግር ዕቅድ ዓላማው፤ ታቅደው-የቀረቡ እና ሁሉን-አካታች እርምጃዎችን አሰባስቦ-የያዘውን በመዘርዘር፣ ወደ ACPS ቋሚ ጠቅላይ-ስራ አስኪያነት የስራ-ድርሻዬ ለመሸጋገር መመሪያ ይሆናል። ይህ ሂደት የተቀረጸው፣ ምንም-ችግር የሌለው ሽግግርን ለማድረግ እንዲያችለኝ - ስለ ማህበረሰባችን እና ክፍላችን/division የሰበሰብኩትን መረጃ በመጠቀም፣ ጠንካራ-የማህበረሰብ አጋርነቶችን እና ግንኙነቶችን በመፍጠር ለመቀጠል፣ ጠብቆ-ለመቆየት - አሁን በምንሰራ ስራ ላይ ለመገንባት - እና የACPS ስራ ከስኬት ጋር ለማጠንከር ሃሳቦችን ለማመንጨት ነው። ይህ ከአጭር-ጊዜ/ረጅም-ጊዜ ራዕይ እና የስልታዊ እቅድ-አወጣጥ ጋር የተያያዘ፤ ተለይተው የወጡ ወሳኝ-የሆኑ ጉዳዮችን እርምጃ-ለመውሰድ፤ እና ሠራተኞቻችንን፣ ማበረሰቦቻችንን እና የመረጃ-ምንጮቻችን እንደገና-አጠናክሮ ለማሳተፍ ነው። ይህ ዕቅድ፤ በ2022-23 የትምህርት ዓመት በእኔ-የጊዜያዊነት ጊዜ-ላይ፣ ስራው እንዲቀጥል በማድረግ ባገኘሁት ልምድ ላይ ልዩ-የሆኑ ስልቶችን የሚዘረዝር እና፣ ACPS ወደሚቀጥለው የስኬት ደረጃ የሚያመጣው-ነው።




የACPS የቆየ-ውርሱን/legacy ለመቀጠል እና ለማሻሻል ቁርጠኝነት የማያሳይ እና፣ እኩልነት-ያለው፣ ከፍተኛ የትምህርት ጥራትን - በሁሉም-መገኘት የሚችል እና ሁሉንም የሚያሳትፍ አድርጎ-ለመስጠት ቃል-እገባለሁ። አሁን-ስለ የትምህርት ቤት ማህበረሰቦች ካለኝ እውቀት ጋር ሆኜ፤ ይህን የመረጃ-ስብስብ (data) በመጠቀም አስፈላጊውን ስራ ለመጀመር እችላለሁ። በACPS ያለኝን-ልምድ ከግምት-ውስጥ በማስገባት፤ በዚህ ቋሚ በሆነው የስራ-ድርሻ፣ ስለ ማህበረሰቡ ወይም የመረጃ-ስብስብ (data)ን ማጥናት አያስፈልገኝም፤ እና በመጪው ዓመታት ውስጥ ክፍሉ/division የበለጠ-ከፍተኛ ደረጃ ላይ እንዲደርስ ወዲያውኑ ማስጀመር እችላለሁ።

# የሽግግር ቀደምት-ነገሮች

ወደ ቀጣዩ ሂደት ወደሆነው፣ ወደቋሚ ስራ-አኪያጅነት የስራ-ድርሻዬ በምገባበት ጊዜ፤ በአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools) ውስጥ፣ ልጆችን የማስተማር - መጨረሻ-ማብቂያ የሌለውን ዓላማችንን ለማሳካት፣ ሦስት ልዩ-የሆኑ ቀደምትነት የሚሰጣቸውን ነገሮችን - አቅርቤአለሁ።

## ባህል እና የትምህርት ቤት ተሞክሮ



ሁሉን ተቀባይነት እና ፍትሃዊ እኩልነት ላይ-ተኮር የሆነው ዋና እሴቶቻችንን ለሟሟላት፤ ተማሪዎች፣ ሠራተኞች፣ እና ቤተሰቦች - ወደ ትምህርት ቤቶቻችን እና ቢሮዎቻችን ሲመጡ የባለቤትነት-ስሜት የሚሰጣቸውን - ባህል እና የትምህርት ቤት ተሞክሮን ለመፍጠር፣ ፈጠራዊ-የሆኑ መንገዶችን በመለየት ላይ በቁርጠኝነት-በመስራት መቆየት-አለብን። ዓላማው፤ የመማር-ፍቅርን ለተማሪዎቻችን የሚያነግሱ ፕሮግራሞችን እና ተነሻሽነቶችን መቅረጽ፣ እና ተማሪዎቻችንን ለማገልገል በአዲስ-መልክ የታደሰ የጋለ-ስሜትን መያዝ-ነው።

- ሁሉም ሠራተኞች
- ተማሪዎች
- የማህበረሰብ አጋሮች

## የቀለም-ትምህርት ውጤታማነት



በመልሶ-ማቋምቃም እና ያልጨረሱትን ትምህርት/learning loss ላይ ከፍተኛ-ትኩረት ከማድረግ ጋር፣ በእነዚህ ቀጣይ ጥቂት ዓመታት ውስጥ - የቀለም ትምህርት ፕሮግራማችንን ለማሳደግ ከፍተኛ-የሆነ እርምጃ መውሰድ ወሳኝ-የሆነ ነገር ነው። በመረጃ-ስብስብ ላይ መሠረት ያደረገ (data-based) ውሳኔ-አሰጣጥን መጠቀም፣ እና በትምህርት ቤት ክፍል/division ዙሪያ - ውጤታማ-ሆነው የሚሰሩ ስርዓቶችን እና ሂደቶችን ማቋቋም፤ ሁሉም ተማሪዎች በቀለም-ትምህርት ስኬትን ለማግኘት እርዳታ-ለማድረግ - ተቀዳሚው-ነገር ነው።

- ተማሪዎች
- የወደፊት ተማሪዎች

## በተደጋጋሚነት ቀሪ-መሆን/ ABSENTEEISM እና የተማሪ ተሣትፎ




በቅርብ ዓመታት ውስጥ፣ በሃገሪቱ ዙሪያ ያሉ ክፍሎች/divisions - በተደጋጋሚነት ቀሪ-መሆን (absenteeism) መጨመሩን ተመልከተዋል፣ እና ጠንካራ ዒላማ-ያደረገ ተማሪዎችን የማሳተፍ ጥረቶች እና እርዳታዎች የሚያስፈልግ ሲሆን፣ ይህም ያልጨረሱትን ትምህርት/learning loss እና በማህበራዊ እና ስሜታዊ ጤናማነት ላይ ምላሽ-ለመስጠት እርዳታ-ማድረግ ያስፈልጋል። በመጨረሻነትም፣ ይህን ለተማሪዎቻችን በወሳኝነት አስፈላጊ የሆነውን-ነገር ምላሽ-ለመስጠት - ተጨማሪ የሆነ ተነሳሽነትን መምራት በጣም-ዋነኛው ነገር ይሆናል።

- ተማሪዎች
- ሠራተኛ

# የፕሮግራሞች ትኩረት

ወደ ቋሚ-የስራ ድርሻዬ በምሸጋገርበት ጊዜ፣ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት ፕሮጀክቶች - በቀጥታ የ'ACPS Strategic Plan: Equity for All'ን በሚደግፈው ላይ፤ የወደፊት-ትኩረትን በማድረግ፣ መስራት-የምጀምር-ይሆናል። በአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools) ውስጥ፣ ከፍተኛ-ችሎታ ካለው ቡድን ጋር በመስራት፣ እነዚህን ፕሮጀክቶች ለማጠናቀቅ - በማዳመጥ፣ በመማር፣ በመምራት፣ ግንኙነትን በመገንባት እና የክፍሉ/divisionን ተቀዳሚነት-ያላቸውን ነገሮች ከፍ-በማድረግ፤ ዓላማችንን እና ራዕያችንን ለማሳካት ወሳኝ-የሆኑትን - ሁሉም ተማሪዎች በሕይወታቸው በኮሌጅ እና በስራ-መስክ ዝግጁ-ለመሆን የሚያስፈልጓቸውን እርዳታዎች በመስጠት - ሂደቱን እመራለሁ። ይህ የሽግግር ወቅትም፤ የቀለም-ትምህርት ዕድገቱን ከፍ-ለማድረግ እና ውጤታማነትን-ለማግኘት፣ የማህበራዊ እና ስሜታዊ ትምህርትን፣ ጤና እና ጤናማነትን ለመደገፍ፤ እንደ የትምህርት ቤት ክፍል/division የት-ላይ እንደምንገኝ ለመገምገም ዕድል-ይሰጠኛል።



# ተሣትፎ እና ግንኙነት/COMMUNICATION

በዚህ የሽግግር ወቅት ውስጥ፣ ለባለድርሻ-አባላቶቻች (stakeholders)ን ያለኝን ቁርጠኝነት ከፍ-አድርጌ በመቀጠል - ከማህበረሰባችን መማር እና ማዳመጥን-እቀጥልበታለሁ። ያለውን-ስብጥር፣ ፍትሃዊ-እኩልነት፣ ሁሉን-ማካተት እና የባለቤትነት ስሜት እንዲኖር እያበረታታን እና አቅፈን-እየሰራት በምንገኝበት-ጊዜ ላይ እያለን፣ የማህበረሰቡን ዕምነት የሚያጠነክረውን፣ ባህል እና አኳሃን/climate ላይ ለመገንባት በቁርጠኝነት እየሰራሁ እቀጥላለሁ። ትኩረት-የተደረገበት ስብሰባዎች አማካኝነት፣ በዚህ የሽግግር ሂደት ወቅት ውስጥ፣ የሚከተሉትን ግለሰቦችን እና ቡድኖች ይሳተፋሉ:

| ሠራተኛ | ተማሪዎች | ቤተሰቦች | ማህበረሰብ |
|---|---|---|---|
| • ማዕከላዊ ቢሮ አስተዳደሮች<br>• የአገልግሎት-ሰጪ (custodial) እና የትምህርት ቤት እና የአመጋገብ አገልግሎቶች ሠራተኞች<br>• መምሪያዎች እና የልዩ-ነገሮች ዙሪያዎች/special areas<br>• የአሌክሳንድርያ የትምህርት ማኅበር (Education Association of Alexandria (EAA)<br>• ተዛማጅ የሆኑ አገልግሎቶች ሠራተኞች<br>• ትምህርት ቤት የኮሚቴ አባላቶች<br>• የትምህርት ቤት ደረጃ አስተዳደር<br>• የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን እና ረዳት ርዕሰ መምህር መምህራን<br>• የተማሪ እርዳታ ቡድኖች<br>• እርዳታ-ሰጪ ሠራተኞች (Support staff)<br>• አስተማሪዎች (PreK-12)<br>• የአስተማሪዎች አድቫይዘሪ ካውንስል (Teachers Advisory Council (TAC)<br>• የመጓጓዣ አገልግሎት | • የሁለተኛ-ደረጃ "Slices with the Supe" ምሣዎችን፣ ማስፋፋት<br>• ከመጀመሪያ-ደረጃ ትምህርት ቤት ጋር፣ "Snacks with the Supe"ን ማስጀመር<br>• የጠቅላይ-ስራ አስኪያጅ የተማሪ አድቫይዘሪ ካውንስ (Superintendent's Student Advisory Council (SSAC) - ለከፍተኛ-ደረጃ ተማሪዎች | • የአሌክሳንድርያ፣ PTAC<br>• የቤተሰብ ቡድኖች እና ድርጅቶች<br>• በሚገባ-ያልተወከሉትን ቡድኖች (underrepresented groups) የሚያገለግሉ ድርጅቶች | • የአሌክሳንድርያ ፖሊስ መምሪያ (Alexandria Police Department)<br>• የአሌክሳንድርያ የእሳት መምሪያ (Alexandria Fire Department)<br>• የንግድ ማህበረሰብ<br>• የሲቪክ ማኅበሮች<br>• የማህበረሰብ አጋሮች<br>• በእምነት-ላይ መሠረት ያደረጉ ድርጅቶች<br>• የከተማ አስተዳደር<br>• የሼሪፍ መምሪያ (Sheriff's Department)<br>• የበጎ-ፈቃድ (Volunteer) ድርጅቶች |

# የምስጋና-መግለጫዎች/ ACKNOWLEDGMENTS


ስራቸው ለዚህ የሽግግር ዕቅድ እውን-እንዲሆን ያደረጉትን እና የአሌክሳንድሪያ ከተማ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (Alexandria City Public Schools) ጊዜያዊ ጠቅላይ-ስራ አስኪያጅነት የስራ-ድርሻዬ ወቅት የረዱኝን - የሚከተሉት ሠዎች ከልብ-የመነጨ ምስጋናዬን ማቅረብ እወዳለሁ:

**የአሌክሳንድርያ ከተማ ትምህርት ቤት ቦርድ አባላቶች**
**የACPS ሲኒየር የአመራርነት ቡድን (Senior Leadership Team (SLT)**
**ቬሮኒካ ቴሌዝ (Veronica Tellez)**
**የACPS ተማሪዎች፣ ሠራተኞች፣ እና ቤተሰቦች**